# ለኢትዮጵያ የሚበጅ የፖለቲካ ስትራተጂ መቀየስ የሁላችን ታሪካዊ ሓላፊነት ነው

ገላውዴዎስ ኣርኣያ

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጠረው የፖለቲካ ቀውስና ያስከተለው የምልአተ ሕዝቡ ስጋት፡ ብሎም የዝቅተኛ ንቃት ላላቸው ዜጎች መደናበር፡ ጽልመተ-ዓለም ኢትዮጵያን በይበልጥ ከፍተኛ ችግር ላይ ጥሏታል ማለት ይቻላል። የችግሩ መንስኤ እኛው ነን፡ የምንፈታውም እኛው ነን። ጠለቅ ያለ ትንታኔና ግንዛቤ እንዲኖረን ግን ሰፋ ባለ መልኩና በግልጽ፡ ማለትም በዝርዝር ኣንዳንድ መሰረታዊና የሚዛመዱ ነጥቦችን መወያየት ይኖርብናል።

ኢትዮጵያን በተመለከተ ከጻፍኳቸው ሓተታዎችና ኣቃቂሮች በርካታዎቹ በኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት፡ ባገራችን ልዑላዊነትና ብሔራዊ ጥቅም ላይ ያተኮሩ ናቸው። እነዚህን ርእሰ-ነገሮች በተደጋጋሚ ስላቀረብኳቸው ኣንዳንድ ሰዎች ቋቅ ሳይላቸውና ሳይሰለቻቸው አልቀረም። ይቅርታ እጠይቃለሁ።

ያገር ጉዳይ ግን ይቅርታ የሚጠየቅበት ኣይደለም፡ ለዚህም ነው ለኢትዮጵያ የሚበጅ ማንኛውም የፖለቲካ ስትራተጂ የሁላችን ሓላፊነት ነው የምለው ያለሁት። እንዲህ ያለ ግዙፍ የፖለቲካ አጀንዳ ለተወሰኑ ሰዎች (ለምሳሌ ምሁራን) ወይም ባለስልጣናት ብቻ ማሸከም አይቻልም። በተለይም ደግሞ አንዳንድ ምሁር ልግምተኛና አውቆ የተኛ በሆነበት ግዜና በስልጣን ላይ ያሉትም ከግል ጥቅማቸውና በትረ-ስልጣናቸው ኣልፈው ያገር ጉዳይን ማስቀደም ባልፈለጉበት ጊዜ ሕዝቡ ሓላፊነቱን ለመሸከም ይገደዳል። ስለሆነም፡ እያንዳንዱ ኢትየጵያዊ፡ በተለይም የፖለቲካ ንቃተ ህሊናው ኣንጻራዊ በሆነ መንገድ የላቀ ከሆነ ታሪካዊ ሓላፊነት መሸከም ኣለበት። የመጀመርያው ከፍተኛ ሓላፊነት እንግዴህ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት መጠበቅ ነው። ያለአንድነት አገርን በሚመለከት (ትምህርት፡ ልማት፡ ጤና፡ ልዑላዊነት ወዘተ) የመወያያ ነጥቦች ይዘን ብንቀርብ ትርጉም አይኖራቸውም፡ እንድያውም ከንቱ ውዳሴና የውሸት ፕሮፓጋንዳ ነው የሚሆኑት። በዚሁ መሰረተ-ዓላማ፡ ማለትም የአንድነት አጀንዳ የምንስማማ ከሆነ (የማንስማማበት መንገድ ደግሞ አይታየኝም) በልዩነታችን ሳይሆን በአንድነታችን ነው ማትኮር ያለብን። ማንኛውም አገር ደግሞ እንደ ልዩ ተቋም ቀጣይነቱ አስተማማኝ ሊሆን የሚችለው የሕዝቡ አንድነት ሲጠነክርና ሲጸና ብቻ ነው። በልዩነታችን ላይ ካተኮርን፡ ጥላቻና አምባጓሮ ካከልንበት ግን እንኳንስ ኢትዮጵያ ልታብብና ልትበለጽግ ይቅርና ህልውናዋም ሳይቀር አጠያያቂ ነው የሚሆነው፡ እንደሃገር የማትቀጥልበት ሁኔታም ሊፈጠር ይችላል፡ በብልሃትና በፖለቲካ ብቃት አንድነታችን ካልጠበቅን ደግሞ ፍርክስክሳችን ሊወጣ ያችላል። የውስጥም (ሰርጎገቦች) የውጭም የኢትዮጵያ ጠላቶች ድል ይቀዳጃሉ።

ከላይ የጠቀስኳቸውን ማስጠንቀቅያዎች ቀቢጸ-ተስፋነትን ነው የምያንጸባርቁት። እኔ ግን በተፈጥሮየ ብሩህ ተስፋ ስለሚታየኝ ኢትዮጵያችንን ከመዓት የሚያድኗት ምንግዜም አሏት የሚል ጽኑ እምነት ነው ያለኝ። ላገር የሚቆረቆሩ ዜጎች ፡ ባሁኑ ግዜ ደከም ባለ መልኩ ቢንቀሳቀሱም ቅሉ፡ አሁንም ቢሆን አሉ። ማንኛውም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ዘርና ጎሳ ሳያነሳና ሳይጠቅስ "ኢትዮጵያ" የሚል መፈክር ብቻ ነው ማንገብ ያለበት፡ ከሁሉም የዘርና ጎሳ ጥቅምና ፖለቲካ የኢትዮጵያ አጀንዳ ነው የበላይነት መያዝ ያለበት። ዘርና ጎሳ ትምህርታዊ በሆኑ የጥናትና ምርምር መድረኮች ካልሆነ በስተቀረ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ እንኳንስ እንደመርሆና ፖሊሲ ሊያራምዳቸው ይቅርና ለውይይትም ቢሆን መቅረብ የለባቸውም ብሎ ያምናል። በአንጻሩ የሕዝብ አንድነት እንዳይደፈርስ በንቃት ይታገላል፡ የሁሉም ብሔሮች እኩልነት ለማረጋገጥ ሌት ተቀን ይጥራል፡ ሁሉንም ብሔሮችና ብሔረሰቦች ያፈቅራል፡ ያከብራል፡ በታሪክ፡ በባህል፡ በኃይማኖት፡

በምጣኔ-ሃብታዊ ግንኙነቶች የተቀራኙ መሆናቸውን በጥልቅ ይገነዘባል። ከሁሉም በላይ ደግሞ፡ አገር ወዳዱ፡ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የአንድ ብሔር ኣባል የሆነውን እንዳጋጣሚ መሆኑን፡ ኢትዮጵያውነት ግን በታሪክ የተገነባ መሆኑን በቅጡ ይገነዘባል። ይህ በቀላል አማርኛ እንዲህ ማለት ነው፦ አንድ ግለሰብ ኢትዮጵያዊ የትግራይ ተወላጅ፡ የአማራ፡ ኦሮሞ፡ ጉራጌ፡ ሲዳማ ወዘተ አባል ሊሆን የቻለው እንዳጋጣሚ እንጂ ሆን ብሎ በእቅድ ከዚሁ ብሔር ልፈጠር ብሎ በመምረጥ አይደለም። እንዲህ ያለ ክስተት ተሰምቶም ታይቶም አይታወቅም፡ ለወደፊትም አይኖርም።

ስለሆነም አንድን ብሔር ወይም የአንድን ብሔር አባላት በደፈናው ማውገዝና መርገም የተሳሳተ ርእዮተዓለም ብቻ ሳይሆን የዝቅተኛ ንቃተ ህሊና አመለካከት ነጸብራቅም ነው። ከዚሁ አጉል ንቃተ ህሊና ጋር የተያያዘ አንዳንድ የአካኪ ዘራፍ ፖለቲካ በተደጋጋሚ ሲስተጋባ ሰምተነዋል። አንድን ህዝብ ወይም ጎሳ በጭፍንና በደፈና የመጥላት ዝንባሌ ምንጩና ሂደቱ በስነ-ልቦናዊ ትንተና ማየቱ ትንሽ ብያዳግትም በግብር ግን ብዙ ግዜ ሲተረጎም አይተነዋል። ለውይይት ይመች ዘንድ እስቲ አንዳንድ ታሪካዊ ምሳሌዎች እንጥቀስ፦

ካፄ ምንሊክ እስከ አፄ ኃይለስላሴ ብሎም እስከ ደርግ የነበሩትን ስርዓቶች ሲተነተኑ አንዳንድ ንቃተ ህሊናቸው ዝቅተኛ የሆነውን የትግራይ፡ የኦሮሞ ወዘተ ተወላጆች ጠቅላላ ያማራን ህዝብ የምያወግዙበት ግዜ ነበር። የላቀ ንቃተ ህሊና ያላቸው የትግራይ፡ የኦሮሞ ወዘተ ተወላጆች ግን ሰፊውን ያማራ ህዝብ በችነፈርና በድህነት ይሰቃይ እንደነበር ከመገንዘባቸውም በላይ ስለዚሁ ጉዳይ (የመደብ ቅራኔ በተመለከተ) ሰፊ ቅስቃሴ አካሂደዋል፡ አስተምረዋል፡ ታግለዋል። ሃቁን ከተናገርን ደግሞ ባፄ ምንሊክና ባፄ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ያማራ ሕዝብ ያገኘው ንጥረነገራዊ ጥቅም የለም፡ ስነ-ልቦናዊ ኩራትና ስሜት ካልሆነ በስተቀረ። በርግጥ ከገዢው መደብ ጋር የተቀራኙ መኳንንት፡ ባለስልጣናት፡ ትላልቅ ባለጸጎችና ነፍጠኞች በድሮው ስርዓት ተጠቃሚዎችና በዝባዦች ነበሩ። ሰፊው ያማራ ህዝብ ግን ድሃና ምዝብር ለመኖሩ የምያጠያይቅ አይደለም። የዚሁ ሓቅ ምስክር በመንዝና ተጉለት፡ በጎጃምና በጎንደር የነበረውና ያለዉን አሰቃቂ ድህነትን ነው።

ያሁኑ የኢትጵያ የፖለቲካ ስርአትም በተመሳሳይ ሁኔታ ነው መገንዘብና መተንተን ያለብን። ያሁኑ የኢህአዲግ መንግስት በህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) የባላይነት እንደሚመራ አንድም ሁለትም የለውም። መንግስቱ ኃይለማርያምን የገለበጠ ኃይል በትግራይ ተወላጆች የሚመራ የኢህአዲግ ሰራዊት ነው። ይህ ማለት ግን ባንዳፍታ የትግራይ ሕዝብ ወይም ትግርኛ ተናጋሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ንጥረነገራዊ ጥቅም ከማግኘቱም በላይ ሌሎቹን ብሔሮች እየመዘበረ ነው ማለት አይደለም። በርግጥ ባለፉት 14 ዓመታት፡ ማለትም ኢህአዲግ ስልጣን ላይ ከተቆናጠጠ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ትግራይ ውስጥ ከዚህ ቀደም ያልነበሩ የልማት ፕሮግራሞች ተዘርግቷል፡ በርካታ ተቋሞችና ፋብሪካዎች ተፈጥረዋል፡ መንገዶች ተዘርግተዋል፡ ልዩ ልዩ ኮለጆችና ዩኒቨሪሲቲዎች ተከፍተዋል። ይህ ማለት ግን የትግራይ ሕዝብ የተለየ ጥቅም አግኝቷል ማለት አይደለም፡ በርግጥ ባለፉት 14 ዓመታት የትግራይ ተወላጆች የሆኑት አዳዲስ (እንደ አማራ፡ ጉራጌ፡ ኦሮሞ ወዘተ) ሃብታሞች ተፈጥረዋል። ሰፊው የትግራይ ሕዝብ ግን አሁንም ቢሆን ከድህነትና ችነፈር መውጣት አልቻለም። ታድያ አንድን ሕዝብ የመጥላትና የማጥላላት ዝንባሌ ከየት የመጣ ነው? ስልጣን እንደሆነ ካንድ ግለሰብ ወደ ሌላ ግለሰብ ወይም ካንድ ቡድን ወደ ሌላ ቡድን (መደብ) ሲተላለፍ ቆየ እንጂ ምልአተ ሕዝቡ (ወይም የአንድን ብሔር ብዙሃን) እንኳንስ በትረ-ስልጣኑን ሊጨብጥና በስልጣን ዙርያም ሓሳብ የሚያቀርብበትና የሚወስንበት ግዜ በፍጹም አልነበረም።

አንድን ብሔር የማጥላላት ወይም አንድን ብሔር ከሌላው ብሔር ጋር ማጋጨት ድሮም ባዔ ኃይለስላሴና በደርግ ግዜ በመጠኑም ቢሆን ተሞክሮ ነበር። በዓመት አንድ ግዜ ጃን ሜዳ ውስጥ "የሕዝብ ግጭቶች" ይካሄዱ ነበር፡ ግን ከዛው ክልል አልፈው ሄደው ኣያውቁም። ኃይለስላሴ ዩኒቨሪሲቲ (አሁን አዲስ አበባ ዩኒቨሪሲቲ) ተማሪዎች በነበርንበት ግዜ አልፎ አልፎ በአደማርያም ላቦራቶሪ ውስጥ በተማሪዎች ዘንድ የጎሳ ግጭቶች ተካሂደዋል፡ ግን ዕድሜ ለዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ማህበር (ኡዝዋ) ያስታራቂ ኮሚቴ ተቋቁሞ ግጭቱ ጋብ እንዲልና ችግሩም እዲፈታ ተደርጓል። በባህርዳርና በሃረር መምህራን ማሰልጠኛም ተመሳይ ችግሮች ተፈጥሮው ነበር፡ ግን ተማሪው ከመቅጽበት መፍትሔ በማበጀት የሕዝብ አንድነት እንዳይደፈርስ ታግሏል።

ከፍ ብየ እንደጠቀስኩት ዞሮ ዞሮ የንቃተ ህሊና ጉዳይ ነው የሚሆነው። በመጨረሻ ’60ዎቹና በመጀመርያ ’70ባዎቹ (እንደ ፈረንጅ አቆጣጠር) የኢትዮጵያ ተማሪዎች የተባበረ ክንድና ኢትዮጵያን የሚወክሉ ማህበራት ፈጥረው ነበር፡ በዛን ግዜ በዘርና ጎሳ ሳንለያይ ትንሽቷ ኢትዮጵያ አዲስ አበባ ዩኒቨሪሲቲ ውስጥ መስርተን ነበርን። ነገር ግን አሁን ላጋጠመን ችግር፡ ለምሳሌ "የብሔሮች የመወሰንና የመገንጠል መብት" (በሕገ መንግስቱ የሰፈረውን) ብሎም ያሁኑ አንድን ሕዝብ የመጥላት በሽታ ባዙር መንገድ ’የመጀመርያው ሓጥያት’ የጠነሰስነው እኛው ነን ማለት ይቻላል። ይህ ሓቅ ለንስሓ ወይም ለጸጸት ብቻ አይደለም የማቀርበው ያለሁት፡ ካለፉት ስሕተቶቻችንን ተምረን ኢትዮጵያን የሚበትን ማንኛውም የፖለቲካ አጀንዳ እንዳናራምድ ለማስታወስ ያህል ብቻ ነው። የብሔሮች መብት እንዳለ ሆኖ፡ ትግላችን ግን በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ያተኮረ መሆን ነበረበት። ግን ምናልባት በዚሁ አስተሳሰባችንና ተግባራችን ላይ አንባቢው ግራ እንዳይጋባ አንድ የጭናግስን ጨዋታ ላጫውታችሁ፦

በ1972 (እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር) አርባ ጠም አከባቢ ፈጥኖ ደራሽ ወታደሮች የስድስት ኪሎ ካምፓስ ከበው ከውስጥም ልደታ አደራሽን ከከበቡ በኃላ የተማሪ ቀንደኛ መሪዎች የሚባሉ ለቅመው ይወስዱና ሆለታ ውስጥ ያጉሩናል፡ ከዛም አጣርተው፡ ቀንደኛ ያልሆነውን ከለቀቁ በኋላ፡ በጦር ሰራዊት ትራኮች ጭነው ይወስዱናል፡ ጭናግስን (ሃርርጌ) 33ኛ ሻለቃ ውስጥ ያጉሩናል። ሌሎች ጓዶቻችን ደግሞ በተመሳሳይ መልክ ቦተር በረሃ ውስጥ ይታሰራሉ።

ለጭናግስን ወታደሮች የተነገራቸው ነገር ቢኖር ግን "ተማሪዎች ረብሸው በጎሳ ተለያይተው ያገሪቷን ጸጥታ ስላደፈረሱ ለእርማት እንዲታሰሩ ተፈርዶባቸዋል" የሚል ነበር። ባንጻሩ የታሰርን ተማሪዎች አብረን ስንጨፍርና የልዩልዩ ብሔሮች ሃገራዊ እስክስታ ስናሳይ ወታደሮቹ በጣም ነበር የገረማቸው፡ ውድያም እኛ ኢትዮጵያን እንደምናስቀድምና በጎሳ እንደማንለያይ አስተማርናቸው፡ ንቃተ ሂሊናቸውም ዳበረ፡ መንግስቱም ስጋት ስላደረበት ተማሪዎችና ወታደሮች በቀጥታ እንዳይገናኙ ትእዛዝ አስተላለፈ። ይህ ሳይሳካለት ሲቀር ደግሞ ለሶስት ወር ያህል ተፈርዶብን የነበረውን ተማሪዎች ከ53 ቀን በኃላ እንድንለቀቅ ተደረገ። ወደ ምስራቃዊ ሰጎን ሃረር ፖሊስ ጣብያ ደግሞ መለሱን፡ እዛም አንድነታችን ስላስመሰከርንና የፖሊስ ንቃተ ህሊናም እንዲጨምር ስላደረግን ወድያው ተለቀን ወደ መጣንበት (አዲስ አበበ) እንድንመለስ ተፈቀደልን። መንግስት ግን ሓለፊነቱን በመዘንጋት ወደ መጣንበት በራሱ ትራኮች ከመውሰዱ ይልቅ አጉል ስንብት በማድረግ ሃረር ከተማ ውስጥ ነበር የጣለን። ስለ አንድነታችንና ያገር ተቆርቋሪነታችንን ያስተዋለ የሃረር ሕዝባችን ግን አሳልፎ አልሰጠንም። ገንዘብ አዋጥቶ ወደ ዲሬዳዋ በታክሲ የምንሄድበት መንገድ ፈጥሮ፡ በባቡር ተሳፍረን አዲስ አበባ ድረስ እንድንሄድም አደረገ። እንዴት ያለ ጨዋ ሕዝብ ነው!

ታድያ እንዲህ ያለ ጨዋ ሕዝብ፡ አኩሪ ታሪክ ያለው፡ ባንድነቱ መጽናት የሚፈልግ፡ በዘር እንዲለያይ ተሞክሮ አሻፈረኝ ያለ፡ ከፍተኛ የሃገር ስሜት ያለው፡ ሰርጎገቦች ባሴሩት ተንኮል

ውስጥ ተነክረን አሳልፈን እንሰጠው? በተለይ ንቃታችን ከፍ ያለና ትምህርት ያለን ሰዎች ኢትዮጵያን ለመበተን የሚካሄደው ማንኛውም ሴራ አጥብቀን ማውገዝና መታገል ይኖርብናል። ታሪካዊ ሓለፊነታችን ነው።

ሌላ ከታሪክ የምንማረው ነገር ቢኖር ቅድመ አያቶቻችን ላንድነታችን የሰሩት ጀብዱና የከፈሉት መስዋእት ነው። እንድያውም ኢትዮጵያ በዓለም ዘንድ ታዋቂነትን ያተረፈችው በታሪክዋ ብቻ ሳይሆን ጀግኖች አባቶቻችን ላገር ነጻነትና ልዑላዊነት ባደረጉት ትግልና መስዋእትነትም ጭምር ነው። በ1896 ዓድዋ ላይ የታየው ጀግንነት ባፍሪቃ ብቻ ሳይሆን ባውሮጳም ሳይቀር አድናቆነትን አትርፏል። አድናቆቱ ግን ኢትዮጵያውያን ድል ስለተቀዳጁ ብቻ ሳይሆን እንደ አንድ ወጥ እንደ አንድ ሕዝብ ስለተሰለፉም ነው። ባልቻ አባነፍሶና ራስ አሉላ፡ ራስ ወሌና ራስ መንገሻ፡ ንጉስ ተክለኃይማኖትና ንጉሰ-ነገስቱ አፄ ምንሊክ፡ ራስ መኮንና ራስ ስብሓት አንድ ላይ መሰለፋቸው የኢትዮጵያን አንድነት ያስመሰከረ ታሪካዊ ሓቅ ነው። ይህ የሚያኮራ ታሪክ ለመጭው ትውልድ የምናስተላልፈው ቅርስ እንጂ የምንረሳውና የምናኮላሸው ከቶ አይሆንም። መሆንም የለበትም። አሁን አንዳንድ ተባዮች፡ ሰርጎ ገቦችና አድርባዮች በኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ተንኮል እየጠመጠሙ መሆናቸውን ከማናቸውም ግዜ በቅጡ ተገንዝበነዋል። ዝም ብለን የምናያቸውም አይሆንም። በተለያየ መንገድና አቅጣጫ፡ ትንሽ ብልሃትና የፖለቲካ ብስለትም በመጨመር አቅማችን በሚፈቅድልን መሰረት መታገል ይኖርብናል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅርቡም ቢሆን ክንዱን አስተባብሮ የኢትዮጵያን ልዑላዊነት ለማስከበር መስዋእት ከፍሏል። ሕዝቡ በጎሳና በዘር ሳይለያይ፡ ኢትዮጵያን በማስቀደም፡ እያንዳንዱ ብሔር ይኸን ያህል ሰው ለማሰለፍ ድርሻችንን ይኸውና ብለው ተማጸኑ። ላገራቸው ክብርና አንድነት ለመስዋእት ሰዎች አሰረከቡ። ከነዚህ ብሔሮች አንዱ የሱማሌ ብሔር ሆኖ በአርአያነት የሚጠቀስ ነው፦ በባድመ አከባቢ የነበረውን ሰራዊት በአርአያነታቸው መሰጡት፡ ለእርድ ከወሰዱዋቸው ፍየሎች መካከል አንድዋን ያርዱና፡ ጥይት ጉሮሮዋ ውስጥ ይከቱና ደም የተቀባውን ጥይት አወጥተው በማውለብለብ ለጠቅለላ ሰራዊታችን "ኢትዮጵያን በዚች ጠብቋት" ብለው ተማጸኑ። ለእንዲህ ያለ ጨዋ ህዝብ ታድያ በጎሳና በዘር እንዲለያይ ተንኮል መሸረቡ ሓጥያት አይሆንምን? ተንኮሉ ግን የተሸረበው አሁን ሳይሆን ቀደም ብሎ ነው። እስቲ ስለዚህም ጉዳይ፡ ለስትራተጂ ቅየሳ ይመችን ዘንድ፡ በመጠኑም ቢሆን ጠቀስ እናድርገው።

የዛሬ ሰላሳ ዓመት አንድ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም ባይ ሰው ባንድ ትንሽ መድረክ (ድርጅቱን ወክሎ) የሚያራምደውን የፖለቲካ እምነት ከገለጸ በኋላ የኢትዮጵያ አንድነትና ትልቅነት ለሚገፋበት አጀንዳ እንቅፋት እንደሆነና አሳሳቢ እንደሆነ ደጋግሞ ያስቀምጠዋል። አንድ በስብሰባው የነበረ ግን ግራ የተጋባ ሰው "ታላቅ ኢትዮጵያ የምታስፈራን ከሆነ ካልተበታተነች ግባችን መምታት አንችልም ማለትህ ነው ወይ?" ብሎ ይጠይቅና ተናጋሪው እንዲህ ብሎ ይመልሳል፦"እኛ ኢትዮጵያ እንድትበተን አንፈልግም፡ ግን ታላቅ ኢትዮጵያ ምንግዜም ታሰጋናለች"

በጣም የገረመኝ ነገር ቢኖር ግን ኢህአዲግ ስልጣን ላይ ከተቆናጠጠ በኃላ የመጀመርያ የሕገ መንግስት ረቂቅ ለውይይት ይቀርብና በኒው ዮርክ ከተማ ቲቸርስ ኮለጅ ኮሎምብያ ዩኒቨርሲቲ ተሰብስበን ረቂቁን ስንተች (ካዳራሹ ውጭ ደግሞ ተቃዋሚ ሰልፈኞች ነበሩ) የብሔሮች መብትና የመገንጥል ጥያቄ አወዛጋቢ መሆኑንን ባንዳንድ ሰዎች ከተገለጸ በኃላ፡ አንዱ ተቺ ሳይታወቀው በድንገት "የብሔሮች የመገንጠል መብት" በሕገ መንግስቱ መስፈር እንዳለበት ከተቸ በኃላ "ኢትዮጵያም እኮ ልትበተን ትችላለች" አለ። እኔም መገረም ብቻ ሳይሆን ደነገጥኩም። የደነገጥኩበትም ምክንያት የዛሬ ሰላሳ ዓመት የሰማሁትና ከላይ የጠቀስኩትን እንደገና ሲደገም በመስማቴ ነው። ሚዛናዊ አመለካከት ላለው ሰው ደግሞ፡ ተጨባጭ ነገር ባይኖርም ቅሉ፡

ኢትዮጵያን ለመበተን የሚንቀሳቀስ ኃይል እንዳለ ይሰማኛል። ይህ ኃይል የፈለገውን ያድርግ ግን አይሳካለትም የሚል እምነት ደግሞ አለኝ፡ ምናልባት ጉዳት ሊያዳርስ የሚችለው ግን እኛ ባንድነታችን ሳንቀረቀር እርስ በራሳችን ስንናቆር ብቻ ነው።

ባንድነታችን ጸንተን ሃገራችንን ከኃላ ቀሪነት ባጭር ግዜ ላማሳደግና ለማልማት ከፈለግን ግን መጀመሪያ እርስ በራሳችን መከባባር ይኖርብናል፡ ሕብረታችን ማጠንከር ይኖርብናል፡ ጸረ ኢትዮጵያ ፖለቲካ የሚያራምዱ ግለሰቦችና ቡድኖች መቃወምና መታገል ይኖርብናል፡ ሕብረታችንን ለማዳከም የሚያሴሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ማውገዝና ማጋለጥ ይኖርብናል፡ ጠባብ ብሔርተኞችና ትምክህተኞችን መታገል ይኖርብናል። ከዚህም ለጥቀን ስለ ኢትዮጵያ አንድነትና የሕዝቡ ሕብረት ሰፊ ቅስቀሳ ማካሄድ እንደ ታሪካዊ ኃላፊነታችን መወጣት አለብን። አንድነታችን በሚመለከት የተሰወረ ወይም የተወሳሰበ ስትራተጂ ሳይሆን በቀላሉ የምንገነዘበው እቅድ ነው ማውጣት ያለብን። በሓሳብ ደረጃ የማቀርባቸው እቅዶች ደግሞ ከሞላ ጎደል የሚከተሉት ናቸው፦

1. አንድነትን ለማጠናከር ባገር ደረጃ ማሰብና በግብርም ማሳየት
2. የጎሳና የዘር አጀንዳ ሁሉ ማስወገድና መታገል
3. የብሔርና የክልል አጀንዳዎች ለአገር-አቀፍ አጀንዳ ተቃራኒንና ተቀናቃኝ መሆን የለባቸውም
4. የጎሳ ብቻ ሳይሆን የኃይማኖትም ጭምር ልዩነቶች ያላግባብ እንዳይዳብሩ ጥንቃቄ ማድረግ፡ ከኦርቶዶክስ ተዋህዶና እስልምና ኃይማኖት ውጭ እምነት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ኃይማኖታቸውና እምነታቸው እንዲከበረላቸው ማድረግ። 'ኃይማኖት የግል፡ አገር የጋራ' መሆኑን አሁንም ቢሆን መዘንጋት የለብንም።
5. ማንኛውም ግዙፍ አገር-አቀፍ አጀንዳ በኩርፍያ መተግበር ስለማይቻል፡ ንቃተ ህሊናቸው ዝቅተኛ ለሆነው ወገኖች፡ በተለይም አንድን ብሔር ነጥሎ ለማስውገድ (ሰላምታም ሳይቀር በመንፈግ) ለሚጥሩ ሁሉ በማስተማር ንቃታቸው የሚዳብርበት መንገድ መፍጠር አለብን። ከፍተኛ ንቃት ያለቸውም ጭምር አክርፏልና በነቀፌታና በጓዳዊ መንፈስ የሚታረሙበት መንገድ መፍጠር አለብን።
6. ሰፊ አገር-አቀፍ አጀንዳ ለመተግበር ከፈለግን ኢትዮጵያውያን በሙሉ የሚሳተፉበት መድረኮችና ማሕበሮች መፍጠር አለብን። የኢትዮጵያውያን ማሕበር ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ነው ከተባለ ደግሞ መዋቅሩ ሆን ተብሎ ልዩ ልዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦችን ያቀፈ መሆን አለበት። ያሁኑ ተቃዋሚ ኃይሎች (ኅብረት፡ ቅንጅት) ከሞላ ጎደል ኅብረ-ብሔር ናቸው ማለት ይቻላል። ኢትዮጵያን ካለው ችግርና ቀውስ ለማዳን ከተፈለገ ግን የድሮ የኢህአፓ መዋቅር እንደ ምሳሌ ማየት አለብን። ከሁሉም የድሮ የፖሊተካ ፓርቲዎች እውነተኛ አገር-አቀፍ ፓርቲ የሚባለው ኢህአፓ ብቻ ነበር (መኤሶም በዚሁ ረገድ ወደ ኢህአፓ ይጠጋል)፡ በፓለቲካ ፕሮግራሙ ብቻ ሳይሆንም ሁሉንም የኢትዮጵያ ብሔሮች ያቀፈ ኢህአፓ ብቻ ነበር። ያሁኑ ፓርቲዎች የድሮው የኢህአፓ መዋቅር ቢከተሉ (ፓርቲው እንከን አልነበረውም ለማለት አይደለም፡ ድክመትም ነበረው) ኢትዮጵያ ከመዓቱ ትወጣለች።
7. በተቻለ መጠን ኢትዮጵያን የሚወክሉ አርማዎችና ምልክቶች እንጂ አንዱን የሕብረተሰባችን አባል የሆነውን ሕዝብ፡ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያስወግዱ አርማዎች ያለማንገብ ይመረጣል። ባሁኑ ግዜ ለምሳሌ የኢትዮጵያን ባንዴራ፡ ኢትዮጵያውያን ባሉበት አከባቢ፡ የትም ቦታ የምናይበት ሁኔታ ተፈጥሯል። መልካም! ባንዴራው ያንድነታችን አርማ ስለሆነ ምንግዜም ብናየው ደስ የሚያሰኝ ነው። ግን የባንዴራው አጠቃቀም ቅጥ እያጣ መጥቷል፡ እንደ ልብስ መልበስ፡ እንደ ኮፍያ መልበስ፡ በመኪና ታርጋ ውስጥ መጨመር፡ ኤምባሲ ይመስል በቤትና ጽሕፈት ቤቶች ደጃፍ ላይ ማውለብለብ ወዘተ በመጠኑም ቢሆን የባንዴራውን ክብር የሚቀንስ ይምስለኛል። ባንዴራ በብሔራዊ መዝሙር ታጅቦ የሚሰቀልና የሚወርድ አርማ

ነው፡ ሃገርን በዓለምአቀፍ ደራጃ የሚወክል ምልክት ነው፡ በበርጨሜ አንጥፈን የምንቀመጥበት ጨርቅ አይደለም። ከዚህ ነጥብ ጋር የተያያዘ በጣም አሳሳቢ የሚሆነው ግን በባንዴራው ላይ ያለውን መስቀል ያነገበ አንበሳን ነው። አንበሳው ምልክታችን ስለሆነ ለወደፊትም (መንግስት ሲቀየር) መልሰን ባንዲራችን ውስጥ ማስቀመጥ ይኖርብናል፡ መስቀሉ ግን አገር-አቀፍ አርማ ስላልሆነ መቅረት ያለበት ነው።

ከላይ የተጠቀሱትን አጠቃላይ ጽንሰ-ሓሳቦች ለውይይት ይመች ዘንድና ስትራተጂን ለመቀየስ እንዲረዳን ያቀረብኳቸው እንጂ በድንጋይ ላይ የተለበዱ ዘለቄታ ያላቸው የፖለቲካ ፕሮግራሞች አይደሉም። ሌላው በጣም አሳሳቢ የሆነውና ካገራችን አንድነት፡ ልዑላዊነትና ብሔራዊ ጥቅም ጋር የተያያዘ ምንግዜም የማይተኙ የኢትዮጵያ የውጭ ደመኛ ጠላቶች እንዳሉም መዘንጋት የለብንም። የጥቁር አባይ ፖለቲካ፡ የአፍሪቃ ቀንድና የመካከለኛው ምስራቅ ፖለቲካ፡ የኢትዮጵያን ታሪክና ቅርስ ለማጥፋት የሚንቀሳቀስ ስውር ኃይል ወዘተ ወዘተ ከመቸውም ግዜ በተጠንቀቅ እንድንቀሳቀስ ያደርገናል። እንዲህ ያለ አደጋና ጠላቶች እያሉ ግን እንዴት እኮ ተደርጎ የጎሳ ፖለቲካ እናራምዳለን? ምን ዓይነት ህሊናና ፍልስፍና ቢኖረን ነው አገራችንን ለጎሳ ፖለቲካ ሴረኞች አሳልፈን የምንሰጠው?

እጅግ ባጣም ያዘቀጡ ወገኖቻችን ካሉበት አዘቅት መውጣት የሚችሉ አይመስለኝ። አጋጣሚ ሆኖ ግን ላገራቸው የሚቀረቀሩ በርካታ ዜጎች ስላሉ ኢትዮጵያ አሁን ከወደቀችበት ማጥ ትወጣለች። ይህ ጽኑ እምነቴና ተስፋየ ነው፡ በግብር የሚተረጎሞው ግን ቀደም ብየ እንደ ጠቀስኩት አገር ወዳዶችና ሰፊው ሕዝብ በመተባበር አገር ወዳድ መንግስት ሲያቋቁሙ ብቻ ነው። አሁን ባመራር ደረጃ ያገር ወዳድ ጉዳይ "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" ቢሆንም ቅሉ የድሮ መሪዎቻችን ግን በሃገር ፍቅር ብቻ ሳይሆን በመስዋእትነታቸውም አድናቆትነትን ያተረፉ ነበሩ። የአሁኑ መሪዎቻችን "ኢትዮጵያ ሃገራችን" ወይም "ኢትዮጵያችን" ሲሉ ሰምተናቸውም አናውቅም። እንዳጋጣሚ ዘንግተውት ነው ወያስ ባህርያቸው በውስጠ ታዋቂነት አግዷቸው ነው? የዛሬ አስር ዓመት አንድ ድሮ የማውቀው ሰው የኢትዮጵያን ፓርላማ ወክሎ ወደ አመሪካ ይመጣና ወደ ነበርኩበት ከተማ ያመራል። በተማሪ ንቅናቄ ግዜ ስለምንተዋወቅ ይደውልልኝና ተገናኘተን የወቅቱን ያገራችን ሁኔታ በሚመለከት ተወያየን። በተለይም ስለብሔሮችና ክልሎች አነሳንና "እባካችሁ ኢትዮጵያን የሚል ነገር ማስቀደም አለባችሁ" ስለው ጸጥ ነው ያለው ፡ መልስም አልሰጠኝም፡ ላልኩት ነገር ምንም አስተያየት ሳይሰጥም ተለያየን። በዚህ ጽሑፍ የማቀርበው ስጋት እንግዴህ ቀደም ብሎ የጀመረ ነው።

ያሁኑ ተቃዋሚ ኃይሎች እንደሆኑም ባንድ ጎሳ ላይ የሚካሄደው ዘመቻ በብቃትና በሚገባ እንዳይካሄድ ሰፊ ቅስቀሳና ትምህርት (እንደ ድሮው የኢትየጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ) አላደረጉም። እነሱ ህዝቡን ካለስተማሩት ማን ሓላፊነቱን ይሸከማል? በኔ አመለካከት በተለይ ኅብረ-ብሔር የሆኑት ተቃዋሚ ኃይሎች የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት በተመለከተና የጎሳዎች መጥላትና ማጥላላት ዘመቻ መጥፋት እንዳለበት የጠፈ ቅስቃሴ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ባንድ በኩል በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኛሉ፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሩዋንዳን መቅሰፍት የሚመኙለት በረከተ-መርገሞችን ያጋልጣሉ።

ነገር ግን፡ ተቃዋሚ ኃይሎች ማንኛውም ለኢትዮጵያ የሚበጅ ስትራተጂ ብቻቸውን ሊቀይሱ አይችሉም፡ ሕዝቡ ካላቀፋቸውና ካልደገፋቸው በስተቀረ። ባሁኑ ግዜ ሰፊው ሕዝብ ብዙ ነገር ተምሯል፡ አገር ወዳዶችና ከሃዲዎችን እየለየና እያበጠረም መጥቷል ማለት ይቻላል። ተቃዋሚ ኃይሎች አገር ወዳዶች መሆናቸውን በቅን መንፈስ ካሳዩና ከቀረቡ ሕዝቡ ከመቅጽበት ይደግፋቸዋል። የሕዝብ ድጋፍ ያለው ማንኛውም ኃይል ደግሞ በትረ-ስልጣኑን ከጨበጠ በኋላ

**ለሃገር የሚበጅ የፖለቲካ አጀንዳ ማውጣት ይችላል፣ አጀንዳውም ዘለቄታ ያለው ይሆናል። የኔ ሕልምና ክስተት ይህ ነው፣ በሂወቴ እያለሁ ማየት የምፈልገው ደግሞ እሱ ብቻ ነው።**

**መልካም ዕድል ለኢትዮጵያ!!**